የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.38
ADDIS ABABA 27th February, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ .....................ገጽ ፲፩ሺ፸፭

## Content

Proclamation No. 1110/2019

Refugees Proclamation ..........I......--Page 11,075

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲/፪ሺ፲፩

## የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ

ኢትዮጵያ ለስደተኞች መጠጊያና ከለላን የምትሰጥ እንዲሁም ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ላሉባቸው ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ የምታበረታታ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ ስደተኞችን በተመለከተ ተቀብላ ያፀደቀቻቸው ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች መኖራቸውና የሃገሪቱ የህግ አካል ማድረጓ፤ እንዲሁም በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን አባል በመሆኗ፤

ከላይ በተጠቀሱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተቀመጡ መብቶችን የያዘ፣ ለስደተኞች የተሻለ ከለላ የሚሰጥና ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያስችል በዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሰረት የተቀረጸ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፣

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፬፻፱/፲፱፻፺፮ ጥቅል የሆነና ያልተዘረዘረ ከመሆኑም በላይ በአሁኑ ወቅት ስደተኞችን አስመልክቶ ያለውን አጠቃላይ ለውጥና አዳጊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን የስደተኞችን አያያዝ ለማሻሻል እንዲያስችል የስደተኞች ጉዳይ አዋጅን እንደገና ማውጣት በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO. 1110 /2019

## REFUGEES PROCLAMATION

**WHEREAS,** Ethiopia is providing asylum and protection to refugees and promoting the search for durable solutions whenever conditions permit;

**WHEREAS,** Ethiopia has ratified International Treaties relating to Refugees and make integral part of the law of the land ; and is party to the OAU Convention Governing the Specific Aspects of Refugee Problems in Africa, done in Addis Ababa;

**WHEREAS,** it is necessary to have a comprehensive legal framework, in accordance with international standards, that contains rights and entitlements embodied in the aforesaid International Conventions, provides better protection to refugees and promotes sustainable solutions;

**WHEREAS,** the existing Refugee Proclamation No. 409/2004 is not painstaking and does not reflect the current overall developments and progresses made in refugee protection, it has become necessary to enact a new Refugees Proclamation to improve, within available means, comprehensive protection and assistance to refugees;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 21.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ኤጀንሲ" ማለት የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፫(፬)(ረ) መሰረት የተቋቋመው የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ማለት ነው፤

፪/ "የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር" ማለት በኢትዮጵያ የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት ነው፤

፫/ "የስደተኞች ኮንቬንሽን" ማለት እ.ኤ.አ ጁላይ ፳፰ ቀን ፩ሺ፱፻፶፩ በጄኔቫ የፀደቀው የስደተኞችን ሁኔታ የሚመለከተው ኮንቬንሽን እና እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፴፩ ቀን ፩ሺ፱፻፷፯ በኒውዮርክ የፀደቀው የስደተኞችን ሁኔታ የሚመለከተው ፕሮቶኮል ማለት ነው፤

፬/ "የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን" ማለት እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር ፲ ቀን ፩ሺ፱፻፷፱ በአዲስ አበባ የፀደቀውና የአፍሪካ ስደተኞችን ችግር የተወሰኑ ገፅታዎች የሚገዛው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን ማለት ነው፤

፭/ "የዜግነት አገር" ማለት ስደተኛው ዜጋ የሆነበት አገር ነው፤

፮/ "የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገር" ማለት አንድ ሰው በቋሚነት ይኖርበትና ከለላ ያገኝበት የነበረ አገር ነው፤

## PART ONE

## General

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Refugees Proclamation No.1110/2019."

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Agency" means the Agency for Refugees and Returnees Affair established as per Article 33(4)(f) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No. 1097/2018;

2/ "United Nations High Commissioner for Refugees" means the Office of the United Nations High Commissioner for Refugees in Ethiopia.

3/ "The Refugee Convention" means the Convention Relating to the Status of Refugees done at Geneva on 28th day of July, 1951,and the Protocol Relating to the Status of Refugees done at New York on 31st day of January, 1967;

4/ "The OAU Refugee Convention" mean the Organization of African Unity Convention Governing the Specific Aspects of the Refugee Problems in Africa, done at Addis Ababa on 10th day of September ,1969;

5/ "Country of Nationality" means a country of which the refugee is a national;

6/ "Country of Former Habitual Residence" means the country in which the person established himself permanently and which enjoyed its protection;

፯/ "ስደተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ወይም አንቀጽ ፳፩ የተጠቀሰውን መስፈርት የሚያሟላ ሰው ነው፤

7/ "Refugee" means any person who fulfils the criteria under the provisions of Article 5 or Article 21 of this Proclamation;

፰/ "ጥገኝነት ጠያቂ" ማለት በድንበር ወይም በጠረፍ ላይ ሆኖ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው የሚጠይቅ መሆኑን ያስታወቀ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ሥልጣን ላለው አካል አመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚጠብቅ ማንኛውም ሰው ወይም የሰዎች ቡድን ነው፤

8/ "Asylum-seeker" means any person or group of persons who presents himself or themselves at the border or frontier or within the territory of Ethiopia seeking refugee status and wait for decision of the Authority;

፱/ "የቤተሰብ አባል" ማለት፡-

ሀ) የስደተኛ ወይም የጥገኝነት ጠያቂ ባል ወይም ሚስት፤

ለ) ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ያላገባ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ፤ ወይም

ሐ) ስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው በመጣበት አገር ሕግ መሠረት የተሰጠው የቤተሰብ ትርጉም እንዲሁም እርስ በርስ ያላቸውን ጥገኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ኤጀንሲው በሚያደርገው ማጣራት እንደ ቤተሰብ የቆጠረው ሰው፤

ነው፡፡

9/ "The Family Members" means:

a) any spouse of the recognized refugee or asylum-seeker;

b) any unmarried child of the recognized refugee or asylum-seeker under the age of eighteen years; or

c/ any person the Agency may consider, upon assessment, as member of a family taking into account the meaning of family in the laws of their country of origin and existence of dependency among them..

፲/ "ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ" ማለት፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና ያገኘ፤ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ስደተኛ ናቸው የተባሉ ሰዎች ቡድን አባል የሆነ፤

ነው፡፡

10/ "Recognized Refugee" means a person who:

a) has been recognized as a refugee in terms of Article 5 of this Proclamation; or

b) is a member of group of persons declared to be refugees in terms of Article 21 of this Proclamation.

፲፩/ "የመታወቂያ ሰነድ" ማለት እውቅና ላገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኤጀንሲው የሚሰጥ እንደ የመታወቂያ ወረቀት፣ የመጓጓዣ ሰነድ፣ የይለፍ ወረቀት፣ የምዝገባ ማረጋገጫ ሰነድ፣ የልደት የምስክር ወረቀት እና ተመሳሳይ ማንነትን የሚገልጹ ሰነዶችን ይመለከታል፤

11/ "Identification Document" means documents, issued by the Agency, to recognized refugees and asylum-seekers, including identity paper, travel document, pass permit, proof of registration, birth certificate or similar documents that attest as to the identity of the bearer;

፲፪/ "ከአካባቢ ማኅበረሰብ ጋር ማዋሃድ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም አመታት በስደት የኖሩ እውቅና ያገኙ ስደተኞች በተናጠልም ይሁን በቡድን በሚጠይቁበት ወቅት ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር ሁለንተናዊ ቁርኝት እንዲኖራቸው ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ አግኝተው ዘላቂ መፍትሔ እስኪያገኙ ድረስ ከዜጎች ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩበት ሂደት ማለት ነው፤

12/ "Local Integration" means a process by which individual refugee or groups of refugees who have lived in Ethiopia for a protracted period are provided, up on their request, with permanent residence permit to facilitate their broader integration with Ethiopian nationals until they fully attain durable solutions to their problems;

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፆታንም ይጨምራል።

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፡-

፩/ በኢትዮጵያ የስደተኝነት ከለላ ለማግኘት ጥያቄ ባቀረበ ወይም የስደተኝነት እውቅና በተሰጠው ሰው፣ እና

፪/ በዚህ አዋጅ መብት በተሰጠው፣ ግዴታ በተጣለበት ወይም በሕጉ አፈጻጸም ላይ ተሳትፎ በሚኖረው ማንኛውም ሰው ላይ፣

ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ጠቅላላ መርሆዎችና መስፈርቶች

**፬. ልዩነት አለማድረግ**

ይህ አዋጅ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በዜግነት፣ በአንድ የኅብረተሰብ ክፍል አባልነት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፭. የስደተኝነት መስፈርት**

፩/ ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በአንድ የኅብረተሰብ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ ወይም በተጨባጭ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልት ወይም ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋቱ ምክንያት ከዜግነት አገሩ የተሰደደና በእነዚሁ ክስተቶች ምክንያት የዜግነት አገሩን ጥበቃ ለማግኘት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፣

ለ/ ዜግነት የሌለው ከሆነ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ በአንድ የተወሰነ ቡድን አባል በመሆኑ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት በእርግጥ ወይም ተጨባጭ ማሳደድ ወይም አደጋ ወይም እንግልትና ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመስጋት ከቀድሞ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራው ለቆ የተሰደደ እና መመለስ ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ፣ ወይም

13/ "Person" means a natural person or a juridical person;

14/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of Application**

Provisions of this Proclamation shall be applicable to any person who:

1/ is a refuge apply for recognition or is a recognized refugee in Ethiopia; and

2/ has a right or is subjected to obligations arising from this Proclamation; or participates in the implementation of this Proclamation.

## PART TWO

## General Principles and Criteria

**4. Non-discrimination**

This Proclamation shall be applied without discrimination as to race, religion, Nationality, membership of a particular social group, political opinion or other similar grounds.

**5. Refugee Criteria**

1/ Any person shall be considered as a refugee where:

a) owing to a well-founded fear of being persecuted for reasons of race, religion, nationality, membership of a particular social group or political opinion he is outside his country of nationality and is unable or, owing to such fear, is unwilling, to avail himself of the protection of that country;

b) not having a nationality and being outside the country of his former habitual residence, he is unable, or owing to a well-founded fear of being persecuted for reasons of race, religion, membership of a particular social group or political opinion, he is unwilling to return to it; or

ሐ/ በውጭ ወረራ፣ በግዛት መያዝ፣ በውጭ አገዛዝ፣ የትውልድ ወይም የዜግነት አገሩን ህዝባዊ ሥርዓት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚያናጋ ከባድ ክስተት ምክንያት ከትውልድ ወይም ከዜግነት አገሩ ውጭ ጥገኝነት ለመጠየቅ ሲል መደበኛ መኖሪያ ሥፍራውን ለመልቀቅ የተገደደ እንደሆነ፤

እንደ ስደተኛ ይቆጠራል፡፡

፪/ አንድ ሰው ከአንድ በላይ ዜግነት ካለው ከእነዚህ አገሮች በአንዱ የሚሰጠውን ከለላ እርግጠኛ ወይም ተጨባጭ ስጋት ሳይኖረው ያለበቂ ምክንያት ያልተጠቀመ ከሆነ የዜግነት አገሩን ጥበቃ እንዳላገኘ አይቆጠርም፡፡

፮. <u>ከአገር መውጣት በኋላ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ስለሚሰጥ የስደተኝነት ዕውቅና</u>

ማንኛዉም ሰው ከዜግነት ወይም ከቀድሞ መኖሪያ አገሩ ከወጣ በኋላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተጠቀሱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እንደስደተኛ ይቆጠራል፡፡

፯. <u>እንደስደተኛ ስላለመቆጠር</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ እንደተደነገገው በሰላምና በሰብዕና ላይ ወንጀል ወይም የጦርነት ወንጀል ስለመፈፀሙ፤

፪/ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ከፖለቲካ ወንጀል ውጭ ሌላ ከባድ ወንጀል ስለመፈፀሙ፤

፫/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወይም የአፍሪካ ህብረት ቻርተር ውስጥ የተካተቱ ዓላማዎችንና መርሆዎችን በመጣስ ጥፋተኛ ስለመሆኑ፤

አሳማኝ ምክንያቶች የተገኙ እንደሆነ እንደስደተኛ አይቆጠርም፡፡

፰. <u>የስደተኝነት ዕውቅናን ስለመሠረዝ እና መሻር</u>

፩/ ኤጀንሲው፡-

c) owing to external aggression, occupation, foreign domination or events seriously disturbing public order in either part or the whole of his country of origin or nationality, he is compelled to leave his place of habitual residence in order to seek refuge in another place outside his country of origin or nationality.

2/ In the case of a person who has more than one nationality, a person shall not be deemed to be lacking the protection of the country of which he is a national if, without any valid reason based on well-founded fear, he has not availed himself of the protection of one of the countries of which he is a national.

6. **<u>Recognizing Refugee Status Sur Place</u>**

A person shall be considered as a refugee where the conditions stipulated under Sub Article (1)(a), (b) or (c) of Article 5 of this Proclamation have taken place after he has left the country of his nationality or habitual residence.

7. **<u>Exclusion from Refugee Status</u>**

Notwithstanding the provisions of Article 5 and 6 of this Proclamation a person shall not be considered as a refugee if there are serious reasons for considering that:

1/ he has committed a crime against peace, a war crime, or a crime against humanity, as defined in the international instrument drawn up to make provision in respect of such crimes;

2/ he has committed a serious, non-political crime prior to his entry into Ethiopia as a refugee; or

3/ he has been guilty of acts contrary to the purposes and principles of the United Nations or the African Union as embodied in their respective Charters.

8. **<u>Cancellation and Revocation of Refugee Status</u>**

1/ The Agency may:

ሀ) የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠው ሰው የስደተኝነት ውሳኔ ሲሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተቀመጡትን የስደተኝነት መስፈርቶች ባለማሟላቱ ምክንያት እንደስደተኛ መቆጠር ያልነበረበት ከሆነ፣ ወይም

ለ) የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠው ሰው የስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ ሲሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተካተቱት እንደስደተኛ የማያስቆጥሩ የስደተኝነት መስፈርቶች ምክንያት እንደስደተኛ መቆጠር ያልነበረበት ከሆነ፣

የስደተኝነት እውቅናውን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

፪/ የስደተኝነት ዕውቅና የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ (፩) እና (፫) ስር የተጠቀሱት እንደስደተኛ እንዳይቆጠር የሚያደርጉ መስፈርቶች ዕውቅናውን ካገኘ በኋላ ተግባራዊ የሚሆኑበት ከሆነ ኤጀንሲው የስደተኝነት ዕውቅናውን ሊሽር ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና ከመሰረዙ ወይም ከመሻሩ በፊት ኤጀንሲው ለስደተኛው ስለሁኔታው በጽሁፍ ሊያስታውቀውና ጉዳዩን እንዲያስረዳ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

፬/ የስደተኝነት ዕውቅናን የማንሳት ወይም የመሻር ውሳኔ ውሳኔው በተላለፈበት ሰው የቤተሰብ አባላት ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቤተሰብ አባሉ በዚህ አዋጅ መሠረት በተናጠል የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ስደተኛ ውሳኔው በጽሁፍ በተገለፀለት በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን የይግባኝ አቤቱታ ሊሰማ ይችላል፡፡

a) cancel the refugee status of a person, if he should not have been considered to be a refugee because the inclusion criteria provided by Article 5 of the Proclamation was not met at the time of the initial decision;

b) cancel the refugee status of a person, if he should not have been considered to be a refugee because the exclusion criteria provided under Article 7 of the Proclamation had not been applied at the time of the initial decision.

2/ The Agency may revoke the refugee status of a person recognized in Ethiopia if it is established that, after he is granted refugee status, the exclusion criteria provided by Article 7 (1) or (3) of this Proclamation applies to the person.

3/ The Agency shall give the person, whose refugee status is cancelled or revoked, a prior written notification and an opportunity to explain about the issue.

4/ The decision to cancel or revoke refugee status by the Agency shall also apply to family members of the person with respect to whom the decision has been made; provided, however, that the family member affected by the decision has a right to submit his individual application for refugee status in accordance with this Proclamation.

5/ Any person aggrieved by the decision of the Agency made in accordance with this article may appeal within sixty days of receiving written notification of the decision to the Appeal Hearing Council established in accordance with this Proclamation.

6/ Notwithstanding the provisions of sub-Article (5) of this Article, the Appeal Hearing Council may hear an appeal filed after the expiry of sixty days if the appellant has justifiable cause for having filed a late appeal.

## ፱. እንደስደተኛ መቆጠር ስለሚያበቃበት ሁኔታ

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በራሱ ፍላጎት በዜግነት አገሩ በሚሰጥ ጥበቃ መልሶ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፣

ለ) ዜግነቱን አጥቶ የነበረ ከሆነ በፈቃደኝነት መልሶ ካገኘ፤

ሐ) የሚደርስበትን ማሳደድ በመፍራት ለቆ በወጣው አገር ወይም በቋሚነት በሚኖርበት አገር ውስጥ ራሱን መልሶ ያቋቋመ እንደሆነ፤

መ) የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ዜግነት አግኝቶ በዚሁ በአዲሱ የዜግነት አገሩ በሚሰጥ ከለላ ተጠቃሚ የሆነ እንደሆነ፤ወይም

ሠ) በስደተኝነት ዕውቅና እንዲያገኝ ምክንያት የነበሩ ሁኔታዎች የቀሩ ወይም የተለወጡ ሆነው በዜግነት አገሩ የሚሰጠውን ከለላ ባለመጠቀም አቋሙ የቀጠለ እንደሆነ፤ወይም ዜግነቱን አጥቶ ከሆነ ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ አልመለስም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የሌለ እንደሆነ፣

እንደስደተኛ መቆጠሩ ቀሪ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሠ) ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፭ ስር በተገለጹ ምክንያቶች በዜግነት አገሩ ወይም በቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገሩ የሚሰጥ ከለላ ለመጠቀም ካለመፈለግ የሚመነጩ አስገዳጅ ምክንያቶችን ማቅረብ በሚችል ስደተኛ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በኤጀንሲው በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ስደተኛ ውሳኔው በጽሁፍ በተገለፀለት በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን የይግባኝ አቤቱታ ሊሰማ ይችላል፡፡

## 9. Cessation of Refugee Status

1/ Any person shall cease to be considered as refugee if:

a) he has voluntarily re-availed himself of the protection of the country of his nationality;

b) having lost his nationality, he has voluntarily re-acquired it;

c) he has voluntarily re-established himself in the country which he left or outside of which he remained owing to fear of persecution;

d) he has acquired the nationality of Ethiopia, or that of another country and enjoys the protection of his new country of nationality; or

e) he can no longer, because the circumstances in connection with which he was recognized as a refugee have ceased to exist, continue to refuse to avail himself of the protection of the country of his nationality: or if he has lost his nationality or has no nationality and is able to return to his country of former habitual residence but continue to refuse to do so.

2/ The provision of Sub-Article (1) (e) of this Article shall not apply, however, to a refugee who is able to invoke compelling reasons arising out of previous persecution as set out in Article 5 of this Proclmation, for refusing to avail himself of the protection of the country of his nationality or country of his former habitual residence.

3/ Any person aggrieved by the decision of the Agency made in accordance with this Article may appeal within sixty days of receiving written notification of the decision to the Appeal Hearing Council established in accordance with this Proclamation.

4/ Notwithstanding the provision of sub-Article (3) of this Article, the Appeal Hearing Council may hear an appeal filed after the expiry of sixty days if the appellant has justifiable cause for having filed a late appeal.

## ፲. <u>የሁኔታዎች መሠረታዊ ለውጥ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ (፩)(ሠ) የተመለከቱት መሠረታዊ ለውጦች በዚህ አዋጅ መሰረት የስደተኝነት ዕውቅና ባገኘው ሰው ወይም ሰዎች የዜግነት አገር ወይም የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታ መከሰቱ ከታመነ ኤጀንሲው ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለዚሁ ተግባር አፈፃፀም ሲባል የሚዘጋጅን ልዩ ሥነ-ሥርዓት መሠረት በማድረግ እንዲሁም በመጀመሪያ የስደተኝነት ዕውቅና ለመስጠት ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተከሰተው ለውጥ ጠባይና በቆይታው ላይ ምርመራና ማጣራት እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

፪/ ከዚሁ ምርመራና ማጣራት በኋላ ኤጀንሲው ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ለሰውየው ወይም ለቡድኑ አባላት የተሰጠው የስደተኝነት ዕውቅና ቀሪ የሚደረግ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ የስደተኝነት ዕዉቅና ቀሪ በሆነበት ስደተኛ ወይም በስደተኞቹ ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲሁም እያንዳንዱ ስደተኛ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው መግለጽ አለበት፡፡

## ፲፩. <u>ተገዶ ስላለመመለስ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ በመከልከሉ ወይም ከኢትዮጵያ ለቆ እንዲወጣ ወይም፣ ወደመጣበት እንዲመለስ በመደረጉ ወይም በማናቸውም ሌላ እርምጃ ምክንያት፡-

ሀ) ዘሩን፣ ኃይማኖቱን፣ ዜግነቱን፣ የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባልነቱን ወይም የፖለቲካ እምነቱን ምክንያት በማድረግ ማሳደድ፣ መሰቃየት ወይም መንገላታት ወደ ሚደርስበት አገር፤ ወይም

ለ) በውጭ ወረራ፣ በግዛት መያዝ፣ በውጭ አገዛዝ ወይም የአገሪቱን ሕዝባዊ ሥርዓት ወይም ፀጥታ በከፊል ወይምሙሉ በሙሉ በከባድ ሁኔታ በሚያናጋ ሁኔታ ህይወቱ፣ አካሉ፣ ስብዕናው ወይም ነፃነቱ አደጋ ላይ ወደሚወድቅበት አገር፣

## 10. <u>Fundamental Change of Circumstances</u>

1/ Where the fundamental changes referred to in Article 9 (1)(e) of this Proclamation are considered to have taken place in a country of nationality or former place of habitual residence of a person or persons recognized as refugees under this Proclamation, the Agency, working in collaboration and coordination with the United Nations High Commissioner for Refugees and subject to such other special procedures as may be established for this purpose, shall initiate an assessment and verification of the nature and durability of the changes having regard to the circumstances which justified the grant of refugee status.

2/ Following such assessment and verification, the Agency shall, in collaboration with the United Nations High Commissioner for Refugees, make a decision as to whether or not the refugee status of the person or group of persons concerned shall be declared to have ceased.

3/ The decision made pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall also set out the consequences and implications for the refugee or refugees affected by the cessation of refugee status, including the right of individual refugees to appeal against the decision.

## 11. <u>Non-Forceful Repatriation</u>

1/ No person shall be refused entry in to Ethiopia or expelled or returned from Ethiopia to any other country or be subject to any similar measure if as a result of such refusal, expulsion or return or any other measure, such person is compelled to return to or remain in a country where:

a) he may be subject to persecution on account of his race, religion, nationality, membership of a particular social group or political opinion: or

b) His life, physical integrity or liberty would be threatened on account of external aggression, occupation, foreign domination or events seriously disturbing public order in part or whole of the country.

እንዲመለስ ወይም በዚያው እንዲቆይ የሚያስገድደው ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አይከለከልም፤ ወይም ከኢትዮጵያ ለቆ እንዲወጣ ወይም ወደ መጣበት እንዲመለስ አይደረግም፡፡

፪/ ለአገር ደህንነት አስጊ ለመሆኑ አሳማኝ ምክንያቶች የተገኙ ከሆነ ወይም ከባድ ወንጀል ፈፅሞ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ መሰረት ለኅብረተሰቡ አደገኛ ነው ተብሎ ጥፋተኛ የተባለ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ ፩ ድንጋጌ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

፫/ ኤጀንሲው ይህን አዋጅና ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ አንድ ሰው ለአገር ደህንነት አስጊ ለመሆኑ ከባድ ምክንያቶች መኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡

2/ The benefit of Sub-Article (1) of this Article may not, however, be claimed by a person whom there are serious reasons for regarding as a danger to the national security, or who having been convicted by a final judgment of a particularly serious crime, constitutes a danger to the community.

3/ The Agency shall, in line with this Proclamation and other laws, ensure whether serious grounds exist for regarding a person as a danger to national security.

## ፲፪. <u>ከአገር ስለማስወጣት</u>

፩/ በብሔራዊ ፀጥታ ወይም በሕዝብ ሠላም ምክንያት ካልሆነ በስተቀር እውቅና ያገኘ ስደተኛ ከአገር እንዲወጣ አይደረግም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከአገር የማስወጣት ትዕዛዝ የሚሰጠው በኤጀንሲው ነው፡፡ኤጀንሲው ትዕዛዙን የሚሰጠው የሕግ ስርዓት በመከተልና ስደተኛው በጉዳዩ ላይ ምላሹን አቅርቦ እንዲያስረዳ በመፍቀድ ይሆናል፡፡

፫/ ማንኛውም ከአገር የማስወጣት ትዕዛዝ ከነምክንያቱ ለስደተኛው በፅሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

፬/ ከአገር እንዲወጣ በታዘዘ ስደተኛ ጥያቄ ሲቀርብ የማስወጣቱ ትዕዛዝ ስደተኛው በሌላ አገር በሕጋዊነት ለመኖር እንዲፈቀድለት ለማመልከት እንዲያስችለው በቂ ለሆነ ጊዜ ሊዘገይ ይችላል፡፡

## 12. <u>Expulsion</u>

1/ A recognized refugee shall not be expelled except on the grounds of national security or public order.

2/ An order to expel, pursuant to this Article, shall be made by the Agency. Such an order shall be reached in accordance with due process of law allowing the concerned refugee to present his case.

3/ Any expulsion order shall be communicated in writing to the refugee along with the reasons for the order.

4/ The execution of any expulsion order may, if the concerned refugee requests, be delayed for a reasonable period to enable such refugee to seek legal admission to another country.

## ፲፫. <u>ለጊዜው በእስር ስለማቆየት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ከአገር እንዲወጣ የታዘዘ ስደተኛ ከአገር እስኪወጣ ድረስ የማስወጣት ትዕዛዙን ለማስፈጸም አስፈላጊ ከሆነ ወይም የሃገሪቱን ደህንነት ለማስጠበቅ ወይም የሕዝቡን ሰላም ለማስከበር ኤጀንሲው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ለጊዜው ሊታሰር ወይም በማረፊያ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 13. <u>Temporary Detention</u>

A refugee whose expulsion has been ordered under Article 12 of this Proclamation may be temporarily arrested or detained pending his expulsion upon the order of the Agency, if such detention is necessary for purposes of executing the expulsion order or to ensure that he does not endanger the national security or public order of Ethiopia.

**፲፬. <u>የቤተሰብ አንድነት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የጥገኝነት ጠያቂው የቤተሰብ አባል የጥገኝነት ጥያቄው ጉዳይ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት ይፈቀድለታል፡፡

፪/ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መግባትና መቆየት ይፈቀድለታል፡፡

፫/ የጥገኝነት ጠያቂው ወይም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛው የቤተሰብ አባላት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉበት ጊዜ ጥገኝነት ጠያቂው ወይም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛው ያለው መብት ተጠቃሚ እና ለግዴታዎቹም ተገዢ ናቸው፡፡

፬/ ይህ አንቀጽ የጥገኝነት ጠያቂ ወይም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ቤተሰብ አባል ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት የስደተኝነት እውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ከማቅረብ አይከለክለውም፡፡

፭/ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የቤተሰብ አባል ጋር አንድ ላይ የመሆን ጥያቄ በጥገኝነት ጠያቂ ወይም ዕውቅና ባገኘ ስደተኛ በሚቀርብበት ጊዜ ኤጀንሲው የቤተሰቡ አባላት አንድ ላይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት</u>

**፲፭. <u>የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በድንበር ላይ ሆኖ ወይም በማንኛውም መግቢያ በር በሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ የገባ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በስደተኝነት ለመቆየት የፈለገ ማንኛውም ሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ የኤጀንሲው ጽህፈት ቤት ወይም ቅርንጫፍ ወይም ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ኤጀንሲው በአመልካቹ ጥያቄ መሰረት ማመልከቻው ዘግይቶ የቀረበው አሳማኝ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ጊዜ ካለፈ በኋላ እንዲያመለክት ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

**14. <u>Unity of the Family</u>**

1/ A family member of an asylum-seeker, as provided for in this Proclamation, shall be permitted to enter and remain in Ethiopia until his case is finally decided.

2/ A family member of a recognized refugee, as provided for in this Proclamation, shall be permitted to enter and remain in Ethiopia.

3/ A family member of an asylum-seeker or recognized refugee in Ethiopia shall be entitled to all the rights and be subject to the duties of the refugee or asylum-seeker.

4/ Nothing in this Article prevents a family member of a recognized refugee or asylum-seeker in Ethiopia from himself applying for a refugee status.

5/ The Agency shall facilitate reunification when requests are made by recognized refugees or asylum-seekers to reunify with their family members within Ethiopia.

## <u>PART THREE</u>

## <u>Procedures for Determination of Refugee Status</u>

**15. <u>Application for Recognition of Refugee Status</u>**

1/ Without prejudice to Article 21 of this Proclamation, any person who is at the frontier or any other entry point or within Ethiopia, whether he has entered the country lawfully or otherwise, and who wishes to remain within the country as a refugee in terms of this Proclamation, shall within thirty days, apply to the nearest Agency office or branch office; or police station.

2/ The Agency may, up on the request of the applicant, accept applications made after the expiry of the period stated under sub-Article (1) of this Article if the late application is due to justifiable reasons.

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻ የተቀበለ ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቻውን ወዲያውኑ ለኤጀንሲው ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማመልከቻውን በአካል ማቅረብ ያልቻለ ጥገኝነት ጠያቂ በሌላ ሰው አማካኝነት እንዲያቀርብ ኤጀንሲው ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

፭/ የቤተሰብ አባላት በግላቸው ማመልከቻ ማቅረብ ካልፈለጉ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ የቀረበ ማመልከቻ በሁሉም የአመልካቹ የቤተሰብ አባላት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡ ከወላጁ ወይም ከአሳዳሪ የተለየ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በራሱ ወይም በአሳዳሪው አማካይነት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፮/ አመልካቹ ኤጀንሲው የሚያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሰጠው መግለጫ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፯/ ማንኛውም ጥገኝነት ጠያቂ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ማመልከቻ ካቀረበ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ሂደቱን ከተወ ኤጀንሲው ማመልከቻውን የማጣራት ሂደቱን ያቋርጣል፡፡

፰/ የስደተኝነት ዕውቅና ለማግኘት ባመለከተ ወይም በማመልከት ላይ በሚገኝ ሰው ላይ አገር ውስጥ በመግባቱ ወይም በአገር ውስጥ በመገኘቱ ምክንያት የወንጀል ክስ አይቀርብም፣አይቀጥልም ወይም ቅጣት አይጣልም፡፡

## ፲፮. በኤጀንሲው ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻን መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ወይም ፮ የተደነገገው መስፈርት መሟላቱን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን ከመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ የስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪/ ኤጀንሲው የቀረበለትን ማመልከቻ ለመወሰን በሚመረምርበት ወቅት፦

3/ The police station receiving the application in accordance with this Article shall, as soon as possible forward the application to the Agency.

4/ The Agency may permit a person to submit his application for refugee status through another person if he is unable to submit his own application due to circumstances beyond his control.

5/ An application for refugee status made in accordance with Sub-Article (1) of this Article is deemed to have been made on behalf of all members of the family of the applicant except where individual members of the family choose to submit behalf separate application. An unaccompanied or separated child may, individually, or through his guardian, lodge an application for refugee status.

6/ The applicant shall complete the relevant forms issued by the Agency and vouch for the truth of the statement therein.

7/ The Agency may discontinue the processing of application for refugee status if the asylum-seeker withdraws or abandons his application.

8/ No criminal charge shall be commenced or continued or penalties be imposed against a person who has applied for refugee status or is about to apply pursuant to this Proclamation on account of his illegal entry and presence in the country.

## 16. Decision by the Agency

1/ The Agency shall examine and decide on the application presented to it in accordance with Article 15 of this Proclamation within six months period of time of registering the application after verifying that the criteria provided under Article 5 or 6 of this Proclamation are fulfilled.

2/ In deciding asylum applications, the Agency shall:

ሀ) አስፈላጊው መረጃ በተለይም ስለዕውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት እና የስደተኞችና የጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችና ግዴታዎች በተመለከተ ለአመልካቹ በሚገባው ቋንቋ የተሰጠው መሆኑን፣

ለ) አመልካቹ ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን፣

ሐ) ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የማመልከቻ አቅራቢውን የፆታ ምርጫ ግምት ውስጥ በማስገባት ብቁ የሆነ አስተርጓሚ መመደቡን፣

መ) ማመልከቻው በሚመረመርበት ወቅት በብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የስደተኞች ጉዳይ ሕጎች ላይ አስፈላጊው ዕውቀት ያለው፣ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ልዩ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት የሚችልና ከማመልከቻ አቅራቢው የፆታ ምርጫ ጋር የሚሄድ ብቁ ባለሙያ መመደቡን፣

ሠ) ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የስደተኝነት ዕውቅና ማመልከቻ በሚመረምርበት እና በሚወስንበት ጊዜ በቀዳሚነት የልጁን መልካም አስተዳደግ እና ጥቅም መከበር ታሳቢ መደረጉን፣

ረ) የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲገኝ መጋበዙን፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ኤጀንሲው በስደተኝነት ማመልከቻ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ እስከምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔውን በሰማ በስድሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የይግባኝ ማመልከቻውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም ይግባኝ ባዩ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከስድሳ ቀናት በኋላ የቀረበን የይግባኝ አቤቱታ ሊሰማ ይችላል፡፡

a) ensure that the applicant is provided with relevant information, in a language he understands, in particular relating to the procedures for refugee status determination and rights and obligations of refugees and asylum-seekers;

b) ensure that the applicant is given reasonable time to present his case;

c) ensure the presence of a qualified interpreter during all the stages of the hearing giving due regard to the applicant's preference to have an interpreter of a particular sex;

d) ensure that the personnel conducting the refugee status determination interview has adequate knowledge of Ethiopian and international refugee laws; is competent to take into account the particular circumstances of asylum-seekers; and is selected having due regard to the applicant's preference to be interviewed by a member of a particular sex;

e) take into primary consideration the best interests of the child when examining and making decision on the application of a minor for refugee status.

f) invite the United Nations High Commissioner for Refugees to participate as an observer.

3/ The Agency shall cause the person concerned to be notified of its decision and the reason thereof in writing;

4/ Any asylum-seeker who is aggrieved by the decision of the Agency may, within sixty days of being notified of such a decision, appeal in writing to the Appeal Hearing Council established in accordance with this Proclamation.

5/ Notwithstanding the provision of sub-Article (4) of this Article, the Appeal Hearing Council may hear an appeal filed after the sixty days if the appellant has justifiable cause for having filed a late appeal.

**፲፯. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ስለመቋቋም**

ኤጀንሲው ከስደተኛነት እውቅና ጋር በተያያዘ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርብን ቅሬታ የሚመለከት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፲፰. የጉባዔው አባላት**

፩/ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኤጀንሲው ተወካይ .....................ሰብሳቢ

ለ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ..........አባል

ሐ) የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ተወካይ ..................................................አባል

መ) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ....አባል

ሠ) የኢሚግሬሽን፣ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶችኤጀንሲ ተወካይ.........................................አባል

፪/ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በታዛቢነት እንዲሳተፍ በኤጀንሲው ይጋበዛል፡፡

፫/ ኤጀንሲው ለጉባዔው ፀሐፊ ይመድባል፡፡

፬/ ኤጀንሲው የጉባዔው አባላት በሃገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የስደተኞች ጉዳይ ሕጎች እንዲሁም በስደተኛ እውቅና አሰጣጥ ውሳኔ መርሆዎች፣ መስፈርቶችና ሥነ-ሥርዓቶች ላይ በቂ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

**፲፱. የጉባዔው ስልጣንና ተግባር**

፩/ ጉባኤው በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ በዘጠና ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪/ ጉባዔው የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፡-

ሀ) አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን አቅርቦ ለማስረዳት በቂ ጊዜ የተሰጠው መሆኑን፣

**17. Establishment of the Appeal Hearing Council**

An Appeal Hearing Council (herein after referred to as the "Council") that reviews the decision of the Agency in relation to recognition of refugee is hereby established under this Proclamation.

**18. Members of the Council**

1/ The Council shall have the following members:

a) The representative of the Agency... ...................................................Chairman

b) The representative of the Ministry of Foreign Affairs..............................Member

c) The representative of the Federal Attorney General.................................... Member

d) The representative of the Federal Police Commission............................... Member

e) The representative of Immigration, Nationality and Vital Events Agency ..................................................Member

2/ The United Nations High Commissioner for Refugees shall be invited by the Agency to participate as an observer.

3/ The Agency shall appoint a secretary for the Council.

4/ The Agency shall facilitate, for members of the Council, to acquire the necessary knowledge and skills related to the relevant National and International refugee laws, and applicable principles, standards and procedures of refugee status determination.

**19. Powers and Functions of the Council**

1/ The Council shall within ninety days decide on appeals submitted to it in accordance with this Proclamation.

2/ In the exercise of its function, the Council shall:

a) ensure that every appellant is given reasonable time to present his case;

ለ) ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የአቤቱታ አቅራቢውን የፆታ ምርጫ ግምት ውስጥ በማስገባት ብቁ አስተርጓሚ መመደቡን፣

ሐ) ከወላጅ ወይም ከአሳዳሪ የተለየ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ጉዳይ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በቀዳሚነት የልጁን መልካም አስተዳደግ እና ጥቅም መከበር ታሳቢ መደረጉን፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ጉባዔው የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መርምሮ የኤጀንሲውን ውሳኔ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል፡፡

፬/ ጉባዔው የሚሰጠውን ውሳኔ ከነምክንያቱ ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

፭/ የጉባዔው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፣ ሆኖም ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለው ብሎ የሚያምን ወገን ውሳኔው በጽሁፍ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

፮/ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

## ፳. ስለመዛግብትና ቃለ ጉባዔዎች አያያዝ

የስደተኝነት ዕውቅናን ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻን የሚመለከቱ መዛግብት እና ቃለ ጉባዔዎች የአመልካቹን ጥበቃና ደህንነት ለአደጋ እንዳያጋልጡ ሆነው በሚስጥርና በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ አለባቸው፡፡

## ፳፩. የቡድን የስደተኝነት ዕውቅና ስለመስጠት

፩/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ የአንድ የሰዎች ቡድን ስደተኞች ናቸው ብሎ ለመወሰን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ሲሰጥ ኤጀንሲው ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመመካከር ውሳኔው ላይ ለመድረስ ምክንያት የሆኑ በጥገኝነት ጠያቂዎቹ የዜግነት አገር ወይም መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራ የተፈጠሩ ክስተቶችን፣ የውሳኔው ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ

b) ensure the presence of a qualified interpreter during all stages of the hearing having due regard to the applicant's preference to have an interpreter of a particular sex;

c) take into primary consideration the best interests of the child when reviewing the appeal petition of minors.

3/ The Council may after examining an appeal confirm, vary or reverse the decision of the Agency.

4/ The Council shall notify the appellant of its decision, and the reason thereof, in writing.

5/ The decision of the Council shall be final; provided, however, that any party claiming error of law may appeal to the Federal Supreme Court within 30 days from the date of receipt of the written decision of the Council.

6/ The Council shall issue its own rules of procedure.

## 20. Records and Minutes

The records and minutes of meetings in relation to application for refugee status shall be kept in a confidential and secure manner so that the safety and security of an asylum-seeker may not be in danger.

## 21. Declaration of Class of Persons as Refugees

1/ The Agency may declare any group of persons that meet the criteria set out in Article 5 of this Proclamation as refugees.

2/ When recognizing a group of asylum-seekers as refugees in accordance with this Article, the Agency shall, in consultation with United Nations High Commissioner for Refugees, issue a detailed Directive containing a description of the events in the country of origin or former habitual residence of the

መስፈርቶችን እንዲሁም ውሳኔው ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጊዜ በመግለጽ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው ውሳኔው ተፈፃሚ ከሚሆንበት የጊዜ ገደብ በፊት ከዜግነት ወይም ከመደበኛ የመኖሪያ አገራቸው የለቀቁ ጥገኝነት ጠያቂዎች የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሠረት የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ለመስጠት ምክንያት የሆኑ ክስተቶች የቀሩ ወይም የተለወጡ መሆኑንና ተጨባጭ ስጋት የመሆናቸው ሁኔታ ማብቃቱን የጥገኝነት ጠያቂዎቹ የመነሻ አገር በተመለከተ የተገኘውን መረጃ ግምት ውስጥ በማስገባትና ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመመካከር ሲያረጋግጥ የቡድን ስደተኝነት ዕውቅና ውሳኔ የመስጠት ሂደቱ ማብቃቱን በመግለጽ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል አራት

## የጥገኝነት ጠያቂዎች እና ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች መብቶችና ግዴታዎች

### ፳፪. አጠቃላይ መብቶችና ግዴታዎች

ማንኛውም ጥገኝነት ጠያቂ እና ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ፡

፩/ በስደተኞች ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን እንዲሁም አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች በተደነገጉ መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል፣ ግዴታዎችን ያከብራል፤

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ላይ ባሉ በማናቸውም ሕጎችና ድንጋጌዎች ይገዛል፡፡

### ፳፫. ኢትዮጵያ ውስጥ የመቆየት መብት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ያመለከተ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ፣ ወይም ማመልከቻው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ እንደሆነ የይግባኝ መብቱ እስኪያበቃ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ይፈቀድለታል፡፡

asylum-seekers underlying the decision, the characteristics of the group of beneficiaries to whom the decision applies and the applicable date of the decision.

3/ Notwithstanding the provission of sub-Article (2) of this Article, the Agency may decide to give group refugee status benefit for those who left their country of origin or former habitual residence prior to the applicable date of the decision.

4/ The Agency shall issue a Directive terminating the group refugee recognition procedure when determining, giving due consideration to country of origin information and in consultation with United Nations High Commissioner for Refugees, that the circumstances which led to the group refugee recognition has ceased to exist.

## PART FOUR

## Rights and Obligations of Asylum-seekers and Recognized Refugees

### 22. General Rights and Obligations

Every recognized refugee and asylum-seeker:

1/ is entitled to the rights and be subjected to the obligations contained in the Refugee Convention, the OAU Refugee Convention and applicable international laws;

2/ shall be subject to the laws and Provisions in force in Ethiopia.

### 23. The Right to Stay in Ethiopia

1/ Any person who has applied for recognition of his status as a refugee pursuant to this Proclamation shall be allowed to remain in Ethiopia until the Agency determines his application; or if his application is unsuccessful, until he exhausts his right of appeal.

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጠው ያቀረበውን ማመልከቻ ከተወ፣ በኤጀንሲው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ካላቀረበ ወይም ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው የይግባኝ አቤቱታውን ካልተቀበለው አግባብነት ባላቸው የኢሚግሬሽን ሕጎች መሠረት ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ግለሰቡ ወደ ሌላ አገር መግባት እንዲችል በቂ ለሆነ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ የመኖር መብት አለው፡፡

## ፳፬. ትምህርት ስለማግኘት

፩/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜጎችን ያክል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን እና በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

፫/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ውጭ በሆኑ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ በተለይም የትምህርት ተደራሽነት፣ የውጭ አገር የትምህርት የምስክር ወረቀቶች፣ ዲፕሎማዎች እና ዲግሪዎችን ዕውቅና የማግኘት፣ የትምህርት ክፍያ ስረዛ እና ነፃ የትምህርት ዕድሎችን ማግኘት በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት ለውጭ አገር ዜጎች ከሚደረገው የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፳፭. የጤና አገልግሎት ስለማግኘት

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛና ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

2/ Without prejudice to the provision of Article 11 of this Proclamation, the person may be subject to removal from the country in accordance with applicable immigration laws if he withdraws or abandons his application for refugee status or fails to submit an appeal against a negative decision of the Agency within the appeal period, or his appeal against the decision of the Agency is rejected by the Appeal Hearing Council.

3/ Notwithstanding the provision of sub-Article (2) of this Article, the person may be allowed to remain in Ethiopia for a reasonable period within which he may be able to seek legal admission to another country.

4/ Every recognized refugee has the right to remain in Ethiopia in accordance with provisions of this Proclamation.

## 24. Access to Education

1/ Every recognized refugee or asylum-seeker shall receive the same treatment as accorded to Ethiopian nationals with respect to access to pre-primary and primary education.

2/ Every recognized refugee and asylum-seeker may have access to secondary education; higher education; technical and vocation education and training; and adult and non-formal education within available resources and subject to the education policy of Ethiopia.

3/ Recognized refugees and asylum-seekers may receive the most favourable treatment as accorded to foreign nationals in respect to education other than primary education, in particular, as regards access to studies, the recognition of foreign school certificates, diplomas and degrees, the remission of fees and charges and the award of scholar ships.

## 25. Access to Health Services

Every recognized refugee and asylum seeker shall have access to available health services in Ethiopia.

## ፳፮. የመስራት መብት

፩/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የቅጥር ስራን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት እንደ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛና ጥቃቅን፣ እደጥበባትና ንግድ የመሳሰሉ ዘርፎች ውስጥ በግል ወይም በቡድን ለመሰማራት ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

፫/ ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ያለው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በሙያው ለመስራት ከፈለገ ለውጪ አገር ዜጎች በተፈቀዱ የስራ መስኮች ውስጥ ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያህል ተጠቃሚ ይደረጋል፡፡

፬/ የኢትዮጵያ መንግስትና ዓለም አቀፍ ህብረተሰቡ በጋራ በሚቀርጿቸው ስደተኞችና ኢትዮጵያውያንን የሚጠቅሙ እንደ አካባቢ ጥበቃ፣ ኢንዱስትሪና አነስተኛና ጥቃቅን ዘርፎች የመሳሰሉ የገጠርና የከተማ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች አብረዋቸው ከሚሰሩ የኢትዮጵያ ዜጎች ጋር ተመሳሳይ አያያዝ ይደረጋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእርሻና የመስኖ መሬት አጠቃቀምን በተመለከተ የሃገሪቱ የመሬት አጠቃቀም ህግ እና የክልሎችን ስምምነት መሠረት በማድረግ በሊዝ ዋጋ የሚፈፀም ሆኖ የሊዝ ዘመኑ በየሰባት ዓመቱ የሚታደስ ይሆናል፡፡

፮/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና ንዑስ አንቀፅ (፭) መሰረት በተገለጹ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፍ ለተመረጠ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ በየአምስት ዓመቱ የሚታደስ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፯/ በስራ ላይ በተሰማሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች እና በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል መድልኦ አይደረግም፡፡

## 26. The Right to Work

1/ Recognized refugees and asylum-seekers shall have the right to engage in wage earning employment in the same circumstance as the most favorable treatment accorded to foreign nationals pursuant to relevant laws.

2/ Every recognized refugee and asylum-seeker shall have the right to engage, individually or in group, in agriculture, industry, small and micro enterprise, handicrafts and commerce, in the same circumstance as the most favorable treatment accorded to foreign nationals pursuant to relevant laws.

3/ Every recognized refugee who has academic credentials authenticated by the competent government authority, and who desires to practice his profession, may be accorded the most favorable treatment as accorded to foreign nationals in areas permitted to foreign nationals.

4/ Recognized refugees and asylum-seekers engaged in rural and urban projects jointly designed by the Ethiopian government and the international community to benefit refugees and Ethiopian nationals, including in environmental protection, industry and small and micro enterprises, shall be given equal treatment as accorded to Ethiopian nationals engaged in the same projects.

5/ Without prejudice to the provisions of sub-Article (4) of this Article, the use of agricultural and irrigable lands shall be made in accordance with national land use laws, and in agreement with Regional States using a land lease system, subject to payment of lease price, for a period renewable every seven years.

6/ The Agency may issue a residence permit, subject to renewal every five year, to any recognized refugee selected to engage in the projects indicated under sub-Articles (4) and (5) of this Article.

7/ There shall not be any discrimination between recognized refugees or asylum-seekers and Ethiopian nationals who are engaged in activities stipulated under this Article.

፰/ አግባብነት ያላቸው መብቶች እና ግዴታዎችን የሚደነግጉ የአገሪቱ ሕጐች በስራ ላይ በሚሰማሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፱/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የአገር ውስጥ የስራ ገበያን ለመከላከል በውጭ አገር ዜጎች ላይ የቅጥር ስራ መብትን አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎች ከኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ጋብቻ በፈፀመ ወይም አንድና ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት የያዘ ልጅ ያለው ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በማንኛውም የሀገር መከላከያ፣ የሀገር ደኅንነት፣ ወይም በውጭ ጉዳይና መሰል የፖለቲካ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጥሮ የመስራት መብት የለውም፡፡

## ፳፯. የመደራጀት መብት

ከፖለቲካ ነፃ በሆኑ እና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ማኅበራት እንዲሁም በሠራተኛ ማኅበራት የመደራጀት መብትን አስመልክቶ ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያህል ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፳፰. የመዘዋወር ነፃነት

፩/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ለውጪ አገር ዜጎች በአጠቃላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሕጎችን ተግባራዊ በማድረግ በመረጠው የአገሪቷ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከአገር የመውጣት ነፃነት አለው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ኤጀንሲው ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎችና አካባቢዎችሊያመቻች ይችላል፡፡ የሚያመቻቸው የመኖሪያ ቦታ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከመጡበት የዜግነት ወይም የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ አገር ተገቢው ርቀት እንዲኖረው በማድረግ መሆን አለበት፡፡

8/ Recognized refugees and asylum-seekers who are engaged in activities stipulated under this Article shall be entitled to the rights conferred and be subjected to the obligations imposed by applicable national laws.

9/ Restrictive measures imposed, by applicable laws, on employment of foreign nationals for the protection of the national labor market shall not be applicable to recognized refugee or asylum seeker who is married to Ethiopian national or has one or more child in possession of Ethiopian nationality.

10/ Notwithstanding to the provisions of this Article, any recognized refugee or asylum-seeker shall have no right to be employed in the National Defense, Security, Foreign Affairs and other similar political establishments.

## 27. Right to Association

Recognized refugees and asylum-seekers have the right to association, as regards non-political and non-profit making associations and trade unions in the same circumstances as the most favorable treatment accorded to foreign nationals pursuant to relevant laws.

## 28. Freedom of Movement

1/ Subject to laws applicable to foreign nationals generally in the same circumstances, every recognized refugee or asylum-seeker has, within the national territory, the right to liberty of movement and freedom to choose his residence, as well the freedom to leave the country at any time he wishes too.

2/ Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Agency may arrange places or areas within which refugee and asylum-seekers may live. The arranged residence place shall be located at a reasonable distance from the border of the country of origin or former habitual residence of the recognized refugees and asylum-seekers.

፫/ ኤጀንሲው ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

**፳፱. <u>ንብረት የማፍራትና የማስተላለፍ መብት</u>**

፩/ እዉቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በባለቤትነት መያዝ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች መብቶችን እንዲሁም ከንብረት ጋር የተያያዘ የኪራይና ሌሎች ውሎች ጋር የሚዛመዱ መብቶችን በሚመለከት ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያህል ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

፪/ እዉቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የአዕምሮዓዊ ንብረቶች ማለትም የፓተንት፣ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች፣ የንግድ ምልክት፣ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍና የመሳሰሉ መብቶችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜጋ የሚያገኘውን መብት ያህል በተመሳሳይ ያገኛሉ፡፡

፫/ ጥገኝነት ጠያቂዎች አግባብነት ባላቸው የጉምሩክ ሕጎች መሰረት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተጣለባቸው ዕቃዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገቡ ይዘውት የሚመጡትን ሃብትና ንብረት ያለቀረጥ እንዲያስገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡

፬/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተጣለባቸው ዕቃዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ መጡበት አገር ሲመለሱ ወይም ወደ ሶስተኛ አገር በሚወጡበት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት የመጡት ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያፈሩትን ሃብትና ንብረት ይዘው እንዲወጡ ይፈቀድላቸዋል፡፡

**፴. <u>ፍትሕ የማግኘት መብት</u>**

፩/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ ከዜጎች እኩል በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡

3/ The Agency may facilitate enabling conditions for recognized refugees and asylum-seekers to use their right of movement.

**29. <u>Right to Acquisition and Transfer of Property</u>**

1/ Recognized refugees and asylum seekers shall be entitled to the most favorable treatment accorded to foreign nationals as regards acquisition of movable or immovable property, to leases and other contracts relating to the property.

2/ Recognized refugees and asylum-seekers shall be treated in the same circumstance as Ethiopian nationals as regards intellectual property rights including patent, copy right and neighboring rights, trademarks, industrial designs, and other similar rights contained in other applicable laws.

3/ Without prejudice to provisions of applicable Customs laws regarding prohibited and restricted imports, asylum seekers shall be allowed to bring their assets and property to Ethiopia free of tariff at the time of their first admission to Ethiopia.

4/ Without prejudice to provisions of applicable laws regarding prohibited and restricted exports, recognized refugees or asylum-seekers, when leaving Ethiopia to their country of origin or third country, shall be allowed to take assets or property they brought to Ethiopia or have acquired in Ethiopia.

**30. <u>Right to Access to Justice</u>**

1/ Every recognized refugee and asylum-seeker shall have the same right as nationals as regard to bringing any justiciable matter to, and to obtain a decision or judgment by, the court or any other competent body with judicial power.

፪/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚሰጡ የሕግ ምክርና የድጋፍ አገልግሎቶችን ሊያገኝ ይችላል፡፡

## ፴፩. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

፩/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የሚጠይቋቸውን መስፈርቶች በማሟላት በኢትዮጵያ መንግሥት ተቀባይነት ያለው ሕጋዊ የውጭ አገር ወይም ዓለም አቀፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክትና ሊሰጠው ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሕጋዊ የውጭ አገር ወይም ዓለም አቀፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት እንዲችል ለመርዳት አስፈላጊውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለመውሰድ ፈቃደኛ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ባላቸው ሕጎች የተቀመጡት መስፈርቶች ሊነሱለት ይችላሉ፡፡

፫/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐች የተቀመጡ መሥፈርቶችን በማሟላት በኤጀንሲው የሚሰጥ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የኢትዮጵያ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የማመልከት እና ተፈላጊውን መመዘኛ ካሟላ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

## ፴፪. የመታወቂያ ወረቀት እና የጉዞ ሰነድ

፩/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ከኢትዮጵያ ውጭ ጉዞ ለማድረግ ለኤጀንሲው በጽሑፍ በማመልከት የጉዞ ሰነድ ማግኘት ይችላል፡፡

2/ Every recognized refugee or asylum-seeker may have access to legal counselling or assistance provided in accordance with the laws of Ethiopia.

## 31. Driver's Qualification Certification License

1/ Subject to fulfilling the requirements stipulated in provisions of applicable laws, every recognized refugee or asylum-seeker in possession of a valid foreign or international driving license recognized by the Government of Ethiopia may apply for and be issued with an equivalent driver's qualification certification license in Ethiopia.

2/ To assist in obtaining an equivalent driver's qualification certification license pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the recognized refugee or asylum-seeker may be exempted from requirements applicable to persons holding valid foreign or international driving license pursuant to relevant laws provided that the refugee is willing to take the necessary qualification tests, as may be required.

3/ every recognized refugee or asylum-seeker has the right to apply to acquire an Ethiopian driver's qualification license using his refugee identification documents issued by the Agency subject to fulfilling the necessary requirements stipulated under relevant provisions of applicable laws.

## 32. Identity Paper and Travel Document

1/ Every recognized refugee or asylum-seeker shall be issued with identity paper attesting to his identity.

2/ Every recognized refugee or asylum-seeker shall be entitled to a travel document for the purpose of travel outside Ethiopia up on written application to the Agency.

፫/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የጉዞ ሰነድ ዝግጅት፣ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና አሰጣጥ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ ዝርዝሮች አግባብነት ባላቸው የኢሚግሬሽን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ በተመለከተው መሠረት ይወሰናል፡፡

## ፴፫. የባንክ እና ፋይናንስ አገልግሎት ስለማግኘት

ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኤጀንሲው የተሰጠውን መታወቂያ ሰነድ ብመጠቀም የባንክ ሒሳብ ደብተር የመክፈት፣ ገንዘብ የማስቀመጥ፣ የማውጣት፣ አግባብነት ባላቸው የሃገሪቱ የፋይናንስ ህጎች መሠረት የማስተላለፍና የመሳሰሉ የባንክ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው፡፡

## ፴፬. የቴሌኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ስለማግኘት

ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በኤጀንሲው የተሰጠውን መታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የቴሌኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

## ፴፭. ራሽን ስለማግኘት

በአቅርቦት እጥረት ምክንያት በራሽን መልክ ምርቶች ለማህበረሰቡ በሚከፋፈሉበት ወቅት ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፴፮. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

ማንኛውም ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ አግባብ ያላቸው የወሳኝ ኩነቶችን በተመለከተ በወጡ ሕጎች መሰረት የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ከዜጎች እኩል የማግኘት መብት አለው፡፡

## ፴፯. ክፍያዎች

፩/ ማንኛውም ዓይነት ቀረጥ፣ ክፍያ ወይም ግብርን በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ያሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ከሚጣለው መጠን በላይ ዕውቅና ባገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ አይጣልም፡፡

3/ The preparation, validity and issuance of refugee travel documents as well as other relevant details thereto of recognized refugees and asylum- seekers shall be determined in accordance with applicable immigration laws as well as international instruments.

## 33. Access to Banking and Financial Services

Every recognized refugee or asylum-seeker has the right to open a personal bank account, deposit, transfer or withdraw money and obtain other banking services in accordance with relevant Ethiopian financial laws using identification document issued by the Agency.

## 34. Access to Telecommunication Services

Every recognized refugee or asylum-seeker has the right to access telecommunication services using the identification document issued by the Agency.

## 35. Rationing

Where a rationing system exists, which regulates the general distribution of products in short supply, recognized refugees and asylum-seekers shall be accorded the same treatment as nationals.

## 36. Vital Events Registration

Every refugee or asylum-seeker shall be treated in the same circumstances as nationals with respect to the registration and issuance of certificate of registration of vital events, in accordance with applicable laws.

## 37. Fiscal Charges

1/ Recognized refugees and asylum-seekers shall not be subject to imposition of any duty, charge or tax, of any description what so ever, higher than imposed on nationals in the same circumstances.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው የመክፈል አቅም ለሌላቸው ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች የመታወቂያ ወረቀት፣ የጉዞ ሰነድ፣ የመውጫ ቪዛና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ያለ ክፍያ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፴፰. ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ስለሚደረግ ልዩ ጥበቃ

ኤጀንሲው፡-

፩/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂ ሴቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ መብቶችና ጥበቃዎችን በተለይም ፆታን መሰረት ካደረገ ጥቃት ጥበቃ ማግኘታቸውን፣

፪/ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂ ህጻናት አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ መብቶችና ጥበቃዎችን በተለይም ከጥቃት፣ ከእንግልት፣ ከብዝበዛና ከሕገወጥ ዝውውር ጥበቃ ማግኘታቸውን፣

፫/ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ለጥቃት ለተጋለጡ ሌሎች ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ፍላጎቶቻቸውን መሰረት ያደረገ እገዛ መደረጉን፣

ያረጋግጣል፡፡

## ፴፱. ዕውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ግዴታዎች

፩/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር፣ በኤጀንሲው ሲጠየቅ አስፈላጊውን መረጃ የመስጠትና በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉ ማናቸውንም ሕጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ የሚኖርበትን አካባቢ ባህል የማክበር እና ከአካባቢው የመልካም አኗኗርና የሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ አካባቢውን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

2/ Without prejudice to the provision of sub-Article (1) of this Article, the Agency may provide, to recognized refugees and asylum-seekers who are unable to pay the prescribed fee, with identity documents, travel documents, exit visas and similar services free of charge.

## 38. Special Protection to Persons who are vulnerable

The Agency shall ensure that:

1/ recognized refugee and asylum-seeker women shall enjoy the rights and protections enshrined under relevant laws in particular, specific measures are taken to protect them from gender based violence.

2/ recognized refugee and asylum-seeker children shall enjoy the rights and protections enshrined under relevant laws in particular; specific measures are taken to protect them from abuse, neglect, exploitation and trafficking.

3/ special protection and assistance to other refugees and asylum-seekers with specific needs is provided commensurate with their needs.

## 39. Obligations of Recognized Refugees and Asylum-seekers

1/ Every recognized refugee and asylum-seeker shall cooperate with the Agency, provide relevant information in respect to their application for refugee status to the Agency when requested and respect the laws in force within Ethiopia.

2/ Every recognized refugee and asylum-seeker shall respect the cultures of the people and refrain from practices repugnant to public morality.

3/ Every recognized refugee and asylum-seeker shall have the duty to protect the environment.

**፵. በፈቃደኝነት ወደ አገር ስለመመለስ**

፩/ ማንኛውም ስደተኛ በራሱ ነፃና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፈቃድ ወደ ዜግነት አገሩ ወይም ወደ ቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታው ደህንነቱና ክብሩ ተጠብቆለት የመመለስ መብት አለው፡፡

፪/ ኤጀንሲው ወደ አገራቸው ለመመለስ ለጠየቁ ስደተኞች ከስደተኞቹ መነሻ አገር፣ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነርና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚቻለውን ያክል ድጋፍ በማድረግ ፈቃዳቸው፣ ደህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ያመቻቻል፡፡

**፵፩. ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ስለማዋሃድ**

ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች በተናጠልም ይሁን በቡድን ጥያቄ ሲያቀርቡ ኤጀንሲው እንዳስፈላጊነቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተዋህደው የሚኖሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**፵፪. ዜግነት ስለማግኘት**

ዜግነትን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ድንጋጌዎች ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የኢትዮጵያን ዜግነት በሕግ ለማግኘት ማመልከት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፫. ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር ስለሚደረግ ትብብር**

የኢትዮጵያ መንግስት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በስደተኞች ኮንቬንሽን አንቀጽ ፴፭ መሰረት ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል ትብብር ያደርጋል፡፡

**፵፬. ሚስጥር መጠበቅ**

ይህን አዋጅ እንዲሁም በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የሚያስፈፅም ማንኛውም ሰው በስራው ምክንያት የሚያገኘውን ከጥገኝነት ጠያቂ ወይም ከስደተኛ ጋር የተያያዘ ማንኛውም መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ

**40. Voluntary Repatriation**

1/ Every recognized refugee has the right to a free and informed choice to seek to repatriate, in safety and with dignity, to his country of nationality or former habitual residence.

2/ The Agency shall, in collaboration with the country of origin, the United Nations High Commissioner for Refugees and other partners, provide every possible assistance to facilitate the voluntary, safe and dignified return of refugees who request repatriation.

**41. Local Integration**

The Agency may, upon their request, as it is necessary facilitate local integration of recognized individual refugee or groups of refugees who have lived in Ethiopia for a protracted period.

**42. Naturalization**

Every recognized refugee or asylum-seeker who fulfills the necessary requirements provided in the relevant provisions of the Ethiopian Nationality Law relating to naturalization may apply.to acquire Ethiopian Nationality by law.

## PART FIVE

## Miscellaneous Provisions

**43. Cooperation with United Nations High Commissioner for Refugees**

The Government of Ethiopia shall co-operate with the United Nations High Commissioner for Refugees in the exercise of its functions in accordance with Article 35 of the Refugee Convention.

**44. Confidentiality Principle**

Any person implementing this Proclamation, and Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation shall have the obligation to safeguard the confidentiality of any information he obtains, in the course of his work related to asylum-seekers or recognized

አለበት፡፡ በተለይም ከስደተኛው ወይም ከጥገኝነት ጠያቂው አገር ባለሥልጣናት ወይም ስቃይ አድርሰዋል ከተባሉ አካላት መረጃ አይሰበስብም፣ መረጃም አሳልፎ አይሰጥም፡፡

## ፵፭. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፬፻፱/፲፱፻፺፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፵፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ኤጀንሲው ይህንን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ ተመስርቶ የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፵፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

refugees, in particular he shall not collect information from or disclose information to the authorities of the country of origin of the recognized refugee or asylum-seeker or any alleged actors of persecution.

## 45. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Refugee Proclamation No. 409/2004 is hereby repealed by this Proclamation.

2/ No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matters provided for in this Proclamation.

## 46. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Agency may issue detailed Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued under this Proclamation.

## 47. Effective date

This Proclamation shall come into force on the date of its Publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 27th day of February, 2019.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት